# ወሬና ውይይትን ለእውቀት ለተግባርና ለውጤት እናድርጋቸው

## ለመወያያ መድረኮቻችን (ክፍል አንድ)

በፍርሀትና በስለላ መረብ ተተብትቦ አንደበታችን ክፉኛ ተሸብቦ ያሰብነውን መናገር ካቆምን ሦስተኛ ትውልድ መምጣቱ ነው። ይህን ሁሉ ሰንሰለት በመበጣጠስ ጎልዳፋው አንደበት እንዲሞረድ የውይይት መድረኮች ታላቅ ጠቀሜታ አላቸው። ጋዜጦች፣ ሬድዮኖችና ድኅረ ገጾች ዜናዎችንና የሀሳብ ጭማቂዎችን በማቅረብ የመረጃ ጥማታችንን ያስታግሱልናል። ይህንን ለማድረግ ለተጉ ወገኖቼ ሁሉ ምስጋናዬን እነሆ። በነኚህ ወገኖችም ምክንያት በርካታ አዋቂዎችና ደፋሮች ወደ መድረክ እየመጡ ነው። በጥንካሬአችን ላይ መረባረብ ወደ ውጤት ይወስደናል ብለን አምነን "የምንፈቅደውን ከመደገፍ እንነሳና ለማጠናከር ደግሞ እንትጋ" እንዳልነው ሁሉ፣ የተፈጠረውን መልካም ስራ ወደበለጠ ውጤታማነት የሚወስደውን መንገድ እናመቻች። ጊዜያቸውን ገንዘባቸውን መስዋዕት አድርገው የተተበተበውን አንደበት እንፈታው ዘንድ የሚያግዙና ብሄራዊ አንደነታችንን ለማስከበር፣ በእኩልነትና በነጻነት፣ በፍቅርና በመቻቻል ለመኖር የሚያበቃንን የነጻነት ጎዳና የሚያበጁ ወንድሞችና እህቶችም ይመስገኑ። በዚህም ጥርጊያ ደፋር ጀግኖች ወደ መድረኩ እንደመጡ ሁሉ እርጋታና ማስተዋልን ተጠቅመን ዐይን አፋርና ፈሪ ጥበበኞችም መድረኩን ይቀላቀሉ ዘንድ እናበረታታቸው። የድፍረትና የጥበብ ውህደትም ነው በጋራ ወደ ዕድገት ጎዳና የሚወስደን።

ወሬ የውይይት መንደርደርያ ወይም ማሟሻ ነው። መረጃ ያለውም የሌለውም፣ በቂ እውቀት ያለውም የሌለውም፣ በምክንያት የሚንደረደረውም በስሜት የሚነዳውም ሁሉ የመሰላቸውን የሚሉበት ነው። ስለዚህ ወሬ ጥሩ ነገር ነው። የመሰለንን ማለት ስንጀምር በውል ማሰብም እንጀምራለን ምክንያቱም የራሳችንን ድምፅ እየሰማን የሌሎችን ፊት ስናነበው የሚያስደስት ወይም የሚቆነጥጥ ነገር ይሰማናል። የሚያደምጡ ስዎች ምላሽም ተጨማሪ ወሬ ይሆነናል። ያወቅነውን መናገር በመቻላችን እራሳችንንም እናስተምራለን። እናም ወሬ የውይይት እርሾ ነው ብንል ይቻለናል። ብዙ ታላላቅ ነገሮች የተሰሩት በመጀመርያ እንደ ቀልድ በወሬ ተጠንስሰው ነው። ወሬ ግን ማደግና መለወጥ ካልቻለና ራሱን ሲደግም ከኖረ ዐየር የሚበክል ጫጫታ ወይም ወረቀት የሚፈጅ የቃላት ክምር ብቻ ይሆናል።

ወሬ የአይነት ለውጥ ማድረግ ከታደለ ወደ ውይይትነት ያድጋል። ውይይት ደግሞ መረጃ አስረግጦ፣ ታሪክ አጣቅሶ መርምሮና መዝኖ የሚኬድበት ሲሆን መነሻና መድረሻ ሊኖረው የሚገባና እንደሁኔታው እውቀት ሊጨበጥበት አቋም ሊያዝበትና የተግባር መመርያም ሊሆን የሚያስችል የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሀሳብ ግንኙነት ይሆናል ማለት ነው።

የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሀሳብ ግንኙነት እንበለው እንጂ ውይይት ከራስም ጋር ይደረጋል። በነሲብ ካደረግናቸው ጉዳዮች ውጪ አብዛኛውን ውሳኔ በግላችን ስንወስን ከራሳችን ጋር ተወያይተን ነው። አእምሮና ልቦና ሁሌም በውይይት የሚያደርጉት ነገር ውጤቱ እንኳ የከፋ ቢሆን ፀፀትና ቁጭት አይገባንም። ምክንያቱም በጊዜው ከዚህ በላይ ማሰብ አልቻልም ነበር ብለን ወደፊት ማየት እንጀምራለንና።

አንድዳንድ ጊዜ ልቦና ያሸነፈ እንደሆንና በዚያም ምክንያት ውሳኔያችን የተሳሳተ ወይም ያሳዘነን ከሆነ በየዋህነትና በቅንነት በማድረጋችን እንደተበለጥን እንቆጥረዋለን።አዕምሮአችን የነገረንን ችላ በማለታችን እናዝናለን እናም "... እያወቅሁት እኮ ነው ...." ብለን እራሳችንን እንወቅሳለን። አእምሮ ብቻውን ያሸነፈ እንደሆን በዚህም ውሳኔ ምክንያት አትራፊና አሸናፊ ብንሆንም እንኳ የምናስተውል ሰዎች ከሆንን በማሸነፋችን ብንደስትም እንኳ በመጨከናችን፣ ችላ ብለን ባለማለፋችንና ነገሩን ባለመተዋችን የተሸነፈው ወይም የተጎዳው ወገን ያሳዝነናል። በማሸነፍ ያደረግነውን በደግነትና በርህራሄ መልሰን ብንሰጥም የማይቆጨን ጊዜ አለ። ዋናው ቁም ነገር ግን የፈለገውን ያህል ግጭትና ጭቅጭቅ ቢያደርጉም አእምሮና ልቦና አብረው ይኖራሉ።

የሁለቱ በውስጣችን መኖርም ሙሉ ሰው ያደርገናል። አንዱ ከአንደኛው ከተለየ ወይ ከሞኝና ከጅል አለያም ከወፈፌ ተራ እንመደባለን። ማኅበራዊ ሕይወታችንም ክፉኛ ይበደላል። እንደ አንድ ሕዝብም የሀሳብ ልዩነታችን የመኖር ምልክታችን መሆኑን መቀበል ብንችልና በሚያራርቀን ጉዳይ ላይ ከምንፎክር በሚያቀራርበን ጉዳይ ላይ ብንመክር ደግ ይሆናል፡ ሰብዕናችን ላይ ሳይሆን ሀሳባችን ላይ ፍትጊያና ፍጭት ቢኖር የሚወጣው እሳት የእውቀት ብርሀንና ጉልበትም ይጨምርልናል እንጂ ሕይወት አይቀጥፍብንም።

ምንም እንኳ ወሬ ጥቅም አለው ብንልም በራሱ ግን ወደ ፍሬ አያደርስም። የተወለካከፈው የኢትዮጵያችን ጉዳይ በአብዛኛው በወሬና በውይይት መካከል ያለውን ልዩነት ባለማወቅና የሚያውቁትም በአግባቡ ሊጠቀሙበት በአንድ ወይም በሌላኛው ምክንያት ባለመፍቀዳቸው ይመስለኛል። በሀገራችን የውይይት ባህል ነበረ። ሽማግሌዎች ውይይትና ክርክርን በአግባቡ ይመሩ እንደነበረ ይነገራል። ትምህርት ቤቶችም ውስጥ ድሮ ድሮ የክርክርና የውይይት ባህል ነበር። ዩኒቨርሲቲ ውስጥም እንደዚያው እንደነበረ የሚነገር ቢሆንም በሀገራችን ውስጥ በስተ መጨረሻ ምክንያታዊነትና ስሜት ቃየልና አቤል የሆኑት ፊደል ቆጠርኩ ባለው ትውልድ ነው። ነጻው

መድረክ የነበረው በመጸዳጃ ቤቶች ብቻ ነበር። እየተጸዳዱ በመቸክቸክ። ስለሀገር የሚጠይቁትን፣ የተለየ ሀሳብ ያላቸውን ነጭ ለባሽ፣ ጆሮ ጠቢ እያሉ ለትምህርትና ለእውቀት ክብር የነበራቸውን ቄስ፣ ባንዳ እያሉ በወሬና በጉልበትም ያዘናጉቱ ናቸው ዛሬ ሀገር እያፈረሱ ያሉት። በዘመነ አብዮት ደግሞ ዋናው ማስፈራርያና አፍ ማስያዣ መፈክር ነበር። ለግማሽ ሰዐት እርግማን ከወረደ በሁዋላ ታጣፊ ክላሽ ጉልበታቸው ላይ ካጋደሙ ካድሬዎች ጋር ነበር በውይይት ስም ድርጅታዊ ማስፈራርያ ሲነገር የነበረው። ሁሉም ላይማሩ የቻሉት የውይይትን በር በመዝጋታቸውና ራሳቸውን ብቻ በመስማታቸው ነበር። በዘመነ ወያኔ የመጣው 'አራዳ ዲሞክራሲ' ደግሞ መናገር የደፈሩ ሀገር ወዳዶችንና አዋቂዎችን መመንጠርያ መሳርያ ነበር የሆነው። የተናገሩም ይሁን የጻፉ በጠላትነት ተፈርጀው ወደ እስርና ስደት ተገፈተሩ። ይህም ወያኔን ወደ መቃብሩ ያፈጥነው ዘንድ እርግጥ ነው። ያሸነፈውም የውይይት ባህል ከሌለው እርስ በርሱ ሲራኮትና ሲራገጥ ይከርማታል።

አሁን ያለው ትውልድ በዚህ የቅስም ስብራት ውስጥ ያለፈ በመሆኑ መወያየት ቢያቅተን ሊፈረድብን አይገባም። በውጭ የምንኖር በአደባባይ ለማውራት እድል ያገኘን ሰዎች ግን ከወሬው ወደ ውይይቱ፣ ከውይይቱ ደግሞ ወደተግባሩ ለማምራት ባንችል ፈቅደን እውቀት ጠልተን ያደረግነው ነውና ወሬ ስንከልስ መኖር እንገደዳለን። ራዕይ ያላቸው የእውቀት መሪዎች ሳይሆኑ የወሬ አጋፋሪዎች ብቻ ቢንጫጩ ልናድግ አይቻለንም።

እንዲያም ሆኖ የውይይት መድረኮች ከወሬ የሚያተርፉት ነገር አለ። ከገመገሙትና በደረጃ ካስቀመጡት የተሳታፊው ፍላጎት ምን እንደሆነ ለመገመት ይረዳል። ይህንንም መሰረት በማድረግ በመጀመርያ በጉዳዩ ላይ ትምህርት የሚሰጥበትን መንገድ በመፈለግ የተሳታፊውን እውቀት ማቀራረብና (ሁሌም ቢሆን መገንዘብ የሚያሻው የማኅበረሰባችን ስብስብ  ቀለም ከጠገበው ፕሮፌሰር ማንበብ መጻፍ በውል እስከማያውቀው ድረስ አንድ የውይይት ማዕድ ላይ ሊቀርብ መቻሉን ነው) ከዚያ በሁዋላ ዓላማና ግብ ወዳለው ውይይት መሄድ ይቻላል።

መልካም ውይይት ሲደረግ ጎልብቶ የሚወጣው የእውቀት ችሎታችን ይሆናል። ሁሉንም አንድ በሚያደርግ ሀገራዊ ጉዳይ ደግሞ የግድ ከስማችን በፊት የሚለጠፈው የክብር ማዕረጋችን ባለ ትልቅ ራዕይ ያደርገናል ማለት አይደለም። የትምህርት ጥቅሙ ሀሳብን ሰብስቦ ጨምቆ በማቅረብ ላይ ነው። ነገር ግን የሀገር ጉዳይ የዶክተርና የኢንጅነር አይደለም፣ የወጣት የአዛውንት ተብሎ አይከፈልም ወይም የተማረና ያልተማረ ተብሎ አይደለደልም።  የሁሉም ነው ሁሉንም እኩል ያገባዋል። ጀግና በትምህርትና በስልጠና የመወለዱን ያህል በጭንቅም ጊዜ ይወለዳል። አሊ በርኬ በጀነራሎች መካከል ገንኖ የወጣ ተራ ሚሊሺያ ነበር። አሊ በርኬ በውስጡ ያለውን እምቅ ችሎታ ጦርነት መጥቶ ባያወጣው ኖሮ እስከነመፈጠሩም የምናውቅ ጥቂት በሆንን ነበር። ከምናውቀውም ቁልቁል የምናየው እንበዛ ይሆናል። የውይይትም ዋጋው ይኸው ነው። በጎልዳፋ አንደበት የሚሰነዘሩ የፈላስፋ እሳቤዎችና ግንዛቤዎች ብዙ ናቸው። ኢትዮጵያውያን በዚያ እንታወቅም ነበር። ጎልዳፋውንም የቀልጣፋውንም አጣጥመን ስናየው ነው እውቀታችን ፍቅርም ክብርም የሚላበሰው ብሎም የሚያጀግነውና ለመስዋዕትነት የሚያዘጋጀው።

ውይይት በተመሳሳይ ስፍራም ይሁን በርቀት (ቴሌ ኮንፈረንስ፣ ፓልቶክ፣ ወዘተ) በሶስት ምክንያቶች ይደረጋል ብዬ አምናለሁ፤

1ኛ. ልምድ ለመለዋወጥ ለመማማርና በአንድ ጉዳይ ላይ እውቀት ለመጨበጥ፤
2ኛ. ወደ ተግባር የሚውስደውን መንገድ ለማወቅ፣ እቅድ ለማውጣትና ሀላፊነት ለመከፋፈል፤
3ኛ. ሁነቶችን፣ ግኝቶችን ለመገምገምና ጥሩና መጥፎውን ለመለየት እርምት ለማድረግ ወይም ውጤት ለማቅረብ።

በሚቀጥሉት ጽሁፎቼ ይህንኑ ለማብራራትና የውይይት አቅማችንን ለማጎልበት አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸውን ነጥቦች ላቀርብ እወዳለሁ። ለመጀመር እንጂ ከአዋቂዎች ተርታ ሆኖ ለማስተማር አይደለም። ይልቁንም የሚያውቁና በሙያው የተካኑ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ቢተጉ ለማበረታትም ጭምር ነው።

እንደትራፊክ ሕግ ሁሉ አሮጌ መኪና የሚነዳም ይሁን አዲስ፣ የጭነት መኪና ይሁን የቤት መንገድ ላይ ሲወጡ ሁሉም የጋራ የሆነ ሕግ መከተል አለባቸው። ያ ካልሆነ በራሳቸውም ሆነ በሌሎች ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ። የዚያኑ ያህል መንገዶችም በሚገባ ተሰርተውና አስፈላጊ የትራፊክ ምልክቶች ተደርገውና መብራቶችም ተሰርተው እግረኛና ባለመኪናውን በሚገባ ማስተናገድ መቻል አለባቸው። ያኔ አደጋ ይቀንሳል። የጥሩንባ ጩኸትና ስድብም አይበረክትም። የትራፊክ ፖሊሶችም በመዘዋወር ይህንኑ ሲያስተባብሩ፣ ሲቆጣጠሩና ስያስከብሩ እንመለከታለን። እኛም እውቀታችን ከፍተኛ ይሁን ዝቅተኛ፣ አንደበታችን የቀለጠፈም ይሁን ቃል በጭንቅ የሚወጣው፣ ሁላችንንም የሚያሳትፈን መድረክ የማስፈለጉን ያህል፣ ይህንኑ ውጤታማ ልናደርግ የምንችልበት መንገዱም፣ ሕጉም የሰለጠነ ትራፊክ ፖሊስም ሊኖረን ይገባል። ያ ሲኖረን ወሬአችንም ሆነ ውይይታችን ውጤታማ ይሆናል።

በሚቀጥሉት ጽሁፎቼ እስክንገናኝ ጣፋጭ ወሬና ውጤት ተኮር ውይይት ይሁንላችሁ።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com